# የኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር በቤጂንግ ተመሰረተ

ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም.፤ ኢትዮጵያ ኤምባሲ፣ ቤጂንግ - በቤጂንግ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ጥር 26 ቀን 2005 ዓ.ም. ባደረጉት ስብሰባ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ ላይ ተወያይተው በሙሉ ድምጽ ያፀደቁት ሲሆን የአመራር አባላትንም መርጠዋል፡፡



ኢትዮጵያና ቻይና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከመሰረቱ 42 አመታት የተቆጠሩ ሲሆን በተለይ ባለፉት አስር አመታት ግንኙነታቸው ከፍተኛ እመርታን አሳይቷል፡፡ የሁለቱን ሀገሮች ሕዝቦች ግንኙነትና መቀራረብ እያሳደጉ ከሚገኙ ዘርፎች አንዱም ትምህርት ነው፡፡

በቻይና መንግስት በሚሰጡ የነፃ የትምህርት እድሎች እንዲሁም ተማሪዎቹ በግላቸው በሚያደርጉት ጥረት ትምህርታቸውን በቻይና የሚከታተሉ ተማሪዎች ቁጥር እያደገ ይገኛል፡፡ ተማሪዎቹ በቻይና ቆይታቸው ከሚቀስሙት ትምህርትና ልምድ ባሻገር በሀገራቸው ገፅታ በገፅታ ግንባታ፣ በቱሪዝም፣ በባህል፣ በንግድና በኢንቨስትመንት ዘርፎች ያሉትን ዕድሎች አመቺ ሁኔታዎችን በማስተዋወቅ ሥራ ላይ ለማሳተፍ ሲያሳዩ የቆዩት እንቅስቃሴ አበረታች እንደነበር ይታወቃል፡፡ይህንኑ ሀገራዊ ስሜት አጠናክሮና ተባብሮ ለመስራት እንዲሁም እርስበርስ ለመደጋገፍ እንዲያስችላቸው ማህበሩን ማቋቋም እንዳስፈለገ በማህበሩ የመመስረቻ ደንብ ላይ ተቀምጧል፡፡

በበአሉ ላይ በቤይጂንግ የሚገኙ የኢትዮጵያ ዲፕሎማቶች የተገኙ ሲሆን፣ በቻይና የኢትዮጵያ ባለሙሉ ስልጣን አምባሳደር ክቡር አምባሳደር ስዩም መስፍን ባስተላለፉት መልእክት የተማሪዎቹ መደራጀት በኢትዮጵያ ከሚገኙ ተማሪዎችና ወጣቶች መደራጀት ጋር ተለይቶ እንደማይታይና በቤይጂንግ የተጀመረው እንቅስቃሴ እንደአርሾ በመሆን በመላው ቻይና እንዲሁም በኤዥያ አህጉር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እያቀፈና እየተስፋፉ እንደሚሄድ ያላቸውን ተስፋ ገልፀዋል፡፡ ተማሪዎቹ የጀመሩት የመደራጀት እንቅስቃሴ በውጭ እስካሉ ድረስ ብቻ ሳይወሰን ወደሀገራቸው ከተመለሱም በኋላ የቀድሞ በቻይና ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች ማህበር በመመስረት ለኢትዮጵያና ቻይና ግንኙነት እንደድልድይ ሆነው መቀጠል እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡ አያይዘውም በማህበሩ አባላት መካከል ያለው መደጋገፍና ሁሉም ተማሪዎች የያዙትን አላማ እንዲያሳኩ ለማድረግ የሚያደርገው ጥረት ለሌሎችም ምሳሌ እንደሚሆን ያላቸውን እምነት ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ኤምባሲው ባለው አቅሙ ሁሉ ተማሪዎቹንና ማህበራቸውን እንደሚደግፍና አብሯቸውም እንደሚሰራ ክቡር አምባሳደር ስዩም ለተማሪዎቹ በድጋሚ ቃል ገብተውላቸዋል፡፡